**በመድኃኔዓለም ቤተክርስትያን**
**የሕንፃ አስተባባሪ ኮሚቴ**
**የህዝብ ግንኙነት ንዑስ ኮሚቴ**
**በየሶስት ወራት የሚዘጋጅ**
**መፅሄት**



# ማዕዶት

አምስተኛ ዕትም መሰከረም
2010 ዓ/ም

## በሜኔሶታ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን አለቃ የመላከ ሰላም መሪጌታ ጌታሁን መኮንን አጭር መልዕክት



# ስፍራ ጠቦናል

ይህ ቃል ሁለተኛ ነገሥት ምዕራፍ ስድስት ቁጥር አንድ ላይ ያለ ህይለ ቃል ሲሆን ይህን ጥያቄ እግዚአብሔርን ያመልኩ የነበሩ የነቢያት ልጆች ለመንፈስ ቅዱስ አባታቸው ለቅዱስ ኤልሳ ያቀረቡት ጥያቄ ነው ። ጥያቄውም ተሰብስበን የምናመልክበት ቦታ ጠቦናል የሚል ነበር። ቤተክርስትያን የተጀመረችው በአብርሃም ድንኳን ነበር ። አብርሃም እግዚአብሔር የሚወደውን ሲፈጽም የነበረ እግዚአብሔርም ፅናቱን ፤ እምነቱ እና በጎ ሀሳቡን በማየት የኢየሱስ ምሳሌ የሆነ ይስሃቅ የሚባል ልጅ እንደሚወልድ በሥላሴነቱ እና በሶስትነቱ ብስራትን ያሰማው በዛች በተከላት እና በጎ ነገር ቢሚፈፀምባት ደንኳን ውስጥ ሲሆን የአባታችን አብርሃም ድንኳን ሥላሴ የባረኳት የመጀመሪያይቷ ቤተክርስትያን በመባል ትታወቃለች ። ሁለተኛዋ ቤተክርስትያን ሙሴ ከአባቱ ከአብርሃም በተማረው መሰረት እግዚአብሔር በደብረ ሲና ፅላቱን ሲሰጠው ያዘጋጀው ደብተራ ኦሪት የምትባል ድንኳን ስትሆን ለብዙ ዘመናት የስደት እና የመከራ ዘመን አልፎ እስራኤላዊያን ምድረ እርዕስት እስኪ ገቡ ድረስ ታቦተ ፅዮን በደብተራ ኦሪት ድንኳን ወስጥ የነበረች ሲሆን ከሙሴም የተተካው ኢያሱም ይህንኑን ነበር ይከተል የነበረው።

መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ዳዊት << እኔ በዝግባ ቤት ተቀምጬ ታቦተ ፅዮን በድንኳን>> እያለ ያዝን ነበር። የመንፈስ አባቱ ነቢዩ ናታን ለምንድ ነው የማታንፃት ሲለው ይህስ ቢሆን እግዚአብሔር ካልፈቀደ ይሆናል ወይ? አባቴ አንተ በመሆንህ ፀልይልኝ ብሎ ጠየቀው። ዳዊት ቤተመቅደሱን እንደማይሰራ የሚሰራው ከእርሱ አብራክ የሚወለደው ልጁ ሰለሞን ሰለመሆኑ ለነቢዩ ናታን ተገልጾለት ይህንኑ ነገረው ።

የመጀመሪያውን ቤተክርስትያን ከድንኳን ወደ ቤተመቅደስ የለወጠው ሰለሞን ሲሆን በአንደኛ ነገሥት ምዕራፍ ስድስት ቁጥር አንድ ላይ ሰለሞን ቤተመቅደስ መስራቱን እና ቤተመቅደስ ሲሰራ ምን መምሰል እንዳለበት በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን ቤተመቅደሳችንን ስናንፅ ይህን ማንበብና መከተል ይገባናል።

በሰለሞን የተመሰረተችው ቤተመቅደስ አንድ ብቻ በመሆኗ በዘመኑ የነበሩ ነቢያት ምዕመናንን በየቦታው እየሰበሰቡ ያስተምሩ የነበሩ ሲሆን በመግቢያችን በሁለተኛ ነገሥት ምዕራፍ ስድስት ቁጥር አንድ ላይ ስፍራ ጠቦናል ብለን በመሪነት የወሰድነው ቃል በጊዜው በነቢዩ ኤልሳ የተሰባሰቡ ምዕመናን የጠየቁት ጥያቄ ነበር።
የክርስቶስ ልጆች ነቢዩ አኤልሳን <<እነሆ በፊትህ የምንቀምበት ስፈራ ጠብቦናል ወደ ዮርዳኖስም እንሂድ ከእኛም እያንዳንዱ ከዚያ ምሶሶ ያምጣ የምንቀመጥበትንም ስፍራ በዚያ እንስራ አሉት። እርሱም ሂዱ አለ ከእነርሱም አንዱ አንተ ደግሞ ከአኛ ከባሪያዎችህ ጋር ለመሄድ ፍቀድ አለ።

እርሱም እሄዳለሁ አለ ከእነርሱም ጋር ሄደ ወደ ዮርዳኖስ በደረሱ ጊዜ እንጨት ቆረጡ። ከእነሱም አንዱ ምሶሶውን ሲቆርጥ የምሳሩ ብረት ወደ ውኋ ውስጥ ወደቀ እርሱም ጌታዬ ሆይ ወየው ወየው የተዋስኩት ነበር ብሎ ጮኸ የእግዚአብሔርም ሰው የወደቀው ወዴት ነው አለ ስፍራውንም አሳየው እንጨትም ቆርጦ በዚያ ጣለው ብረቱም ተንሳፈፈ። እርሱም ውሰደው አለ እጁንም ዘርግቶ ወሰደው :: >> ሁለተኛ ነገሥት ምዕራፍ ስድስት ቁጥር ሁለት

ዛሬም የእኛ ጥያቄ ልክ እንደ እዛ ዘመን ሰዎች ስፍራ ጠቦናል ሲሆን ።፡የእግዚአብሔርን ቤት ስንሰራ ሁሉ ነገር እንዲሁ አልጋ በአልጋ ያለመሆኑ ብዙ ፈተና ሊገጥም እንደሚቻል የኤልሳ ሰዎች ዛፍ ሊቆርጡበት የነበረው የምሳር ብረት ወደ ባህር መግባት ፈተናን በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን በትዕግስት በፀሎትና በፅናት እነሱ አንድተወጡት ሁሉ ዛሬም እኛም ስፍራ ጠቦናል ስንል ብዙ ፈተናዎች እንደሚገጥሙን አውቀን በፈተናዎች ሳንበገር ካህናቱ በፀሎት ምዕመናኑ በጽናት ልንተጋ ይገባናል። የዛሬ ሃያ አምስት አመታት በጥቂት ሰዎች ተመስርታ ዛሬ በዛ ያሉ ምዕመናን አፍርታ ልክ እንድ ኤልሳ ዘመን ሰዎች ስፍራ ጠቦናል ያለች የደብረ ሰላም ቤተክርስትያናችን በዛ ዘመን የነበረች የፀሎት ስፍራ ነች ቢባል ማጋነን አይሆንም።

# የሕንፃ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቀመንበር መልዕክት

የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ከጊዜ ወደ ጊዜ በምታበረክተው አገልግሎት ረገድ መሻሻልና ዕድገት በማሳየቷ የአባላትና የተከታዮቿ ብዛት እንዲሁም የህጻናትና ታዳጊ ወጣቶች ቁጥር ከግምት በላይ በማደግ ላይ ይገኛል። ይልቁንም በካህናት አባቶችና በመምህሮቻችን የሚሰጠው የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት እንዲሁም የስብከተ ወንጌል ትምህርት ብዙዎችን እየሳበ ከመሆኑም በላይ ልዩ ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ ብዙ ተከታዮችና ተሳታፊዎች በማፍራት ላይ ይገኛል።

ይህ በበረከት የተሞላው አገልግሎት የማደጉን ያህል ቤተክርስትያናችን ግን ባላት የቦታ ውሱንነት ሁሉን ምዕመናን በሚገባ ማስተናገድ አልቻለችም።ይህን የተረዳችው ቤተክርስትያናችን ጥቂት ለማይባል ዓመታት ሰፋ ያለ አብዛኛውን ምዕመን ለማስተናገድ የሚችል ቤተክርስትያን ለመግዛት ወይም ለመስራት ብታቅድም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ወደ ተግባር የሚያሰገባ የተመቻቸ ሁኔታ እልነበረም።

ጠቢቡ ንጉስ ሰለሞን “ለሁሉም ጊዜ አለው” እንዳለው ሁሉ በመድኃኔዓለም ፈቃድ አሁን ባለው የባላደራዎች አስተዳደር ቦርድ አነሳሽነትና መሪነት የሕንፃ እስተባባሪ ኮሚቴ ሥራውን ከጀመረ እነሆ ወራት አስቆጥሯል ። እንደ ዕድልም ሆኖ በቤተክርስትያናችን የቅርብ ዕርቀት ለአዲሱ ሕንፃ መሥሪያ ቦታ በመድኃኔዓለም ታዐምር ማንም ባልጠበቀው ሁኔታ 2.7 ኤካር ስፋት ያለው መሬት በመገኘቱና በአጭር ግዜ ውስጥ ግዥው በመጠናቀቁ ለታሰበው የግንባታ ሥራ ታላቅ እምርታን ሰጥቷል።

ይልቁንም የቤተክርስትያናችን መሥራች አባት ብፅዑ ወቅዱስ አቡነ ዳንኤል የድሬዳዋና የጅቡቲ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ በተገኙበት የአዲሱ ቤተክርስትያን የመሰረት ድንጋይ በታላቅ ክብርና ሥነስረዓት በመቀመጡና በብፁዕ አባታችን በመባረኩ ልዩ ፤ ታሪካዊ ና ለቤተክርስትያናችንና ለምዕመኖቿ ታላቅ ክብርና መንፈሳዊ ኩራትን ያጎናፀፈ የድል ጉዞ ቅምሻ ነበር ማለት ይቻላል።


የደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተክርስትያን የሕንፃ አስተዳደር ኮሚቴ ከያዛቸው ዘርፈ ብዙ ስራዎች መካከል የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ አንዱና ዋናው ሲሆን ተግባሩም በህንፃ ግንባታ ዙሪያ ያሉ መረጃዎችን ለምዕመናን ግልጽና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ መሰጠትና ምዕመናንም ትክክለኛ ግንዛቤ ኖሯቸው የሕንፃ ስራውን በሙሉ ሃይል ማለትም በዕውቀት፤ በገንዘብ፤ በጉልበት እና በጊዜ እገልግሎት እንዲደግፉ ማድረግ ነው።

ይህንንም መሰረት በማድረግ ከዚህ ቀደም “እናስተዋውቃችሁ” በሚል ርዕስ አንድ ህትመት ያቀረበ ሲሆን እነሆ አሁንም ቋሚነት ያለው በቤተክርስትያናችን ግንባታ ና እንቅስቃሴ ይዘት ላይ የሚያተኩር በየሶስት ወሩ የሚታተም “ማዕዶት” በሚል መጠሪያ ሰም መጽሄት አዘጋጅተናል። ማዕዶት የምትጎለብተው የሁላችንም ተሳትፎ ሲታከልበት እና የባለቤትነት ድርሻችንን በተሳትፎ ስናበለፅግ ሰለሆነ ማዕዶትን ከእኛ ፤ ለእኛ፤ በእኛ በማድረግ ለቤተክርስትያናችን ህንፃ ግንባታና ለአጠቃላይ ዕድገታችን ስንል እንጠቀምበት እላለሁ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በጋሻው ካብትይመር ( ኮ/ል)
የሕንፃ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቀመንበር

# እናስተዋውቃችሁ



የዛሬው እንግዳችን በቤትክርስትያናችን የህንጻ አስተባባሪ ኮሚቴ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ እያደርጉ የሚገኙና ይህ ተሳትፏቸው በብዙሃን ዘንድ ተወዳጅነትንና አድናቆትን የተቸራቸው ሰው ናቸው። ብዙዎች እያደረጉ ያሉትን ጥረት፤ እያሳዩ ያሉትን ፍላጎት፤ትጋትና መስዋዕትነት የአመራር ችሎታቸውን እሰየው ብለውላቸዋል ። በእውነቱም በቤተክርስትያናችን የግንባታ እንቅስቃሴ ዙሪያ የቤተክርስትያኗን ህዝባዊ መገናኛ ገጾች ለተከታተለ እንግዳችን እያደርጉ ያሉትን ጥረት ለማድነቅ ግር ሊለው አይችልም ። ለግንባታውም የሚያስፈልገውን የገንዘብ ማፈላለግ ስራ ለማፋጠን የሚደረገውን ጥረት የሚያሰተባብሩበት ዘዴና የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች ይዘት በህብረት፤ በመተሳሰብና በፍቅር ላይ ያነጣጠረ እና እንዲሁም መከባበርና ፈቃደኝነት መሰረት ያደረገ ነው። የህንጻው ግንባታ ሊሳካ የሚችለው በፍቅር የተሳሰረ ቤተሰባዊነት በቤተክርስትያን አባላትና ምዕመናን መካከል ሲፀርስ እንደሆ እና የተያዘው ጥረት የህንጻ ግንባታ ብቻ ሳይሆን የምዕመን ወንድሞች እና እህቶችን የመንፈስ አንድነት መገንባት ጭምር መሆኑን አጽንተው ይናገራሉ ። እንግዳችን የቤተክርስትያናችን የሕንጻ ግንባታ ግብር ሃይል ገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ዶክተር አሻግሬ አጥሬ ናቸው ።ማዕዶት ከዶክተር አሻግሬ ጋር በህይወታቸው ዙሪያና በኮሚቴው እንቅስቃሴ ላይ ቆይታ አድርጋ ለአጋሮቻቸው እና ለምዕመናን ያላቸውን ክብር ፤ ለስራው ያላቸውን ቁርጠኝነት እና ተንሳሽነት ለመመልከት ስትችል በህይወታቸው ዙሪያና በኮሚቴው እንቅስቃሴ ላይ ያደረገችው ውይይት ይህን ይመስላል።

**ማዕዶት፤** ዶክተር አሻግሬ ማን ናቸው ?

**ዶክተር አሻግሬ፥** ስለ እራሴ መናገር ከባድ ነው ሰላሳ ሶስት ዓመታት በዚህ ሀገር ኖሪያልሁ ትውልዴም ከፋ ክፍለ ሀገር ኩሉኮንታ የሚባል ቦታ ሲሆን ከአራት አመት ዕድሜዬ ጀምሮ ያደኩት አዲስ አበባ ነው። ያሳደጉኝ የወላጅ አባቴ ታናሽ እህት አክስቴና የአክስቴ ባለቤት ሲሆኑ የምጠራውም በአክስቴ ባለቤት ስም ነው። ከእነዚህ ወላጆቼ የተማርኩት ዛሬም በህይወት መርህነት የምከተለው ነገር ቢኖር ደግነትን ፤ መፈቃቀርንና መተሳሰብን ነው ። በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ከሶስተኛ ክፍል እስከ አስራሁለተኛ የተማርኩ ሲሆን የከፍተኛ ትምህርቴን የተከታተልኩት በግሪክ ነበር። ሰው ያስባል አምላክ ይፈጽማል እንደሚባለው በተማርኩበት ትምህርት አልሰራሁበትም ።፡ህይወቴን የምመራው በንግድ ውስጥ በመሰማራት ነው።

**ማዕዶት፡** በአንድ ወቅት የቤትክርስትያናችን አለቃ መሪጌታ ጌታሁን መኮንን የሚያደርጉትን ጥረት በማድነቅ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የራሱ ሰው ያዘጋጀል ዶክተር አሻግሬ ለቤተክርስትያናችን ወቅታዊ ሥራ የተመረጡ ናቸው ሲሉ ተደምጠዋል በዚህ አነጋገር ምን ይሰማዎታል?

**ዶክተር አሻግሬ ፤** ንግግሩ ከባድና ትልቅ ሸክም ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም እኩል ይወዳል ማንንም አይለይም እኔ ቤተክርስትያኗን ካገለገሉት ወይም እያገለገሉ ካሉ አባላት የተለየውሁ አይደለሁም እግዚአብሔር እኔን ለይቶ መርጦኛል ብዬ አላምንም። ቤተክርስትያኗን ለ25 ዓመታት አውቃታለሁ በእዚህ ቤተክርስትያን ወስጥ እኔና ባለቤቴ በጋራ ሁለት ልጆች በእራሴ ሁለት ልጆች ክርስትና አንስቻለሁ ከቤተክርስትያኗ በተለያየ ጊዜ ብዙ ግልጋሎት አግኝቻለሁ ግን ቤተክርስትያኗን አገልግያለሁ ወይ ብዬ ስጠይቅ መልሱ አላገለገልኩም ሲሆን አሁን ግን የእግዚአብሔር ፍቃድ ሆኖ እድሉን አግኝቻለሁ ጊዜውም ተመቻችቶልኛል የተለየ ልዩ ችሎታ ግን የለኝም። አባታችን ስላመሰገኑኝ አመሰግናለው።

**ማዕዶት** ፡ በቤተክርስትያን ግንባታ ሂደት በፈቃደኝነት ገብተው እየተሳተፉ ነው እንዴት አገኙት?

**ዶክተር አሻግሬ ፡** እኔ ወደ እዚህ ሰራ የገባሁት አስቤበትም አይደለም ነገሩ የሆነው ባአጋጣሚ ነው። ወደ እዚህ እንድገባ ያደረገኝ አንዲዓለም እምሩ (ገብሬ) ነው ። የቤተክርስትያን ግንባታ መጀመሩን ነግሮኝ ተሳተፍ ብሎ ጠይቆኝ ነው።፡ ቤተክርስትያኗን የማገልገል ዕድል የተከፈተው በዚህ አጋጣሚ ሲሆን ወዳጄ እንዱአለም ወደ ጥሩ ተግባር ሰለመራኝ አመስግነዋለሁ።

**ማዕዶት** ዶክተር አሻግሬ ከፍተኛ አገልግሎት እያደረጉ ነው ሲሉ ብዙ ሰዎች ይደመጣሉ ። የኮሚቴው አባላትም በስራዎ ምክንያት በዚህ ዕትም ላይ እንዲወጡ ድጋፍ ሰጥተዎታል ምን ይሰማዎታል?

**ዶክተር አሻግሬ** እኔ የተለየ ችሎታ የለኝም ከሌላው የተለየ የማደርገው ነገር የለም የማደርገው ነገር ሰውን ማነቃቃት ነው።

**ማዕዶት** ፡ በፈንድሬዚንግ ኮሚቴ እንቅስቃሴ እየተደርገ ነው ምን ግብ ጥላችኋል? ምን ያህልስ ተሳክቶላችኋል? አካሄዱስ እንዴት ነው ?

**ዶክተር አሻግሬ** አሁን የምናስበውን ቤተክርስትያን እስከ ተጨማሪ ኮምፐሌክስ ለመስራት ብዙ ገንዘብ ያስፈልጋል ይህ ደረጃ በደረጃ የሚደረግ ነው ። የቤተክርስትያናችን አባላት 450 ናቸው ይሁን እንጂ የአባላቶቻችን ፋይናንሻል አቅም እኩል አይደለም የአብዛኛው ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ ነው አብዛኛው አባል ልጅ በማሳደግ ፤ ልጆቹን ኮሌጅ በማስተማር ፤ሀገር ቤት ያሉ ወገኖቹን በመርዳት የተጠመደ ነው። ለምሳሌ አሁን የተስማማንበትን የገንዘብ መዋጮ አራት መቶ ሀምሳውም አባላት ቢከፍሉ የሚሰበሰበው ገንዘብ 2.25 ሚሊዮን ዶለር ይሆናል ይህ እንኳን ቢሆን የምንፈልገውን አይሰራልንም። በየጊዜው ከአባላት በሚገኝ ገንዘብ የሚፈለገውን ዕቅድ ማከናውን አይቻልም እንዴት አድርገን የአባላቱን ሸክም እናቃል የሚለው ጥያቄ የኮሚቴያችን ና የሁላችንም ጭንቀት ነው ። ገንዘብ በመንግስት ፤ በግል ድርጅቶች ና በፌድራል መንግስት እጅ አለ ትልቁ ሥራ እንዴት አድርገን እናምጣው ነው ። በዚሁ መሰረት በታርጌት ፊልድ አሁን ደግሞ በዩኤስ ባንክ ስታዲዮም ግላጋሎትን እየሰጠን ለቤተክርስትያናችን ግንባታ ገንዘብ የምናሰባስብበት ፕሮግራም ተጀምሯል። ባለፉት 13 ጨዋታዎች 26000 ዶላር አስገብተናል። በዚህ ፕሮጀክት ላይ እየተሳተፉ ያሉት ሲሶ የሚሆኑ አባላት ሲሆኑ ይህን ተሳትፎ በሶስት እጥፍ ብንጨምረው ገቢያችን በሶስት እጅ ሊያድግ ይችላል። ታርጌት ፊልድ በቀን በሰው 60 ዶለር ቫይኪንግ ደግሞ 100 ዶለር ይከፍላል። እነዚህን ቁጥሮች ስሌት ውስጥ በማስገባት ያለንን እድል ማስላት ይቻላል። የገንዘብ የማሰባሰቡ ሂደት በተለያዩ መንገዶች እየተካሄደ ሲሆን እስካሁን የተጣለባቸውን ገንዘብ መክፈል የጀመሩ አባላት 60 ብቻ ናቸው።። ሽያጭን በሚመለከት በምሳሌነት ስለ እንጀራ ልናገር ስንጀምር 60 እንጀራ እናመጣ ነበር መሸጥ ሰለአልቻልን የምናመጣውን ወደ 40 ቀነስን በየሳምንቱ ከሁለት መቶ በላይ ምዕመናን እየተገኙ 40 መሸጥ እልቻልንም ትብብሩ ብዙ ይቀረዋል ።

**ማዕዶት፡** የአባላትን የበጎ ሥራ ግልጋሎት ለመጨመር ምን እየተሰራ ነው? አባላትስ ምን ማድረግ እለባቸው?

**ዶክተር አሻግሬ፡** በእኛ በኩል በየጊዜው እያሳሰብን የምናውቃቸውን እያስማማን የተሳታፊዎችን ቁጥር ለመጨመር እየጣርን ነው። ኑሮን ለማሸነፍ የሚደርገው መሯሯጥ ፤ ጠንካራ የነፃ አገልግሎት ልምድ አለመኖር ፤ የተለያዩ ማህበራዊ ዝግጅቶች ጊዜ በመሻማታቸው እና ችላ ማለት ምክንያቶች ሲሆኑ ይህንን ትልቅ ምግባር ዳር ለማድረስ መነሳሳት የሚገባ በመሆኑ ያልተመዘገባን እንድንመዘግብ ይህን ግልጋሎት ለሌሎች በስጦታ መልክ የምናበርክትበትን እና በአቅመ ደካሞች ስም በመስራት ከበረከቱ ተካፋይ እንዲሆኑ የማደርግ ባህልም ሊዳብር ይገባዋል ።

**ማዕዶት** ፡ አሁን እርሶ የሚሰሩት ሥራ ትግስትን የሚፈታተን ይመስላል ትግስቱን ከየት አገኙት?

**ዶክተር አሻግሬ ፡** ለትግስት ዕድሜ ትልቅ አስተዋጾ አለው። አምላክ በሰጠኝ ጭንቅላት እኩራራ ነበር በዚህ ምክንያት ውድቀቶችም ደርሰውብኛል። በውድቀት ጊዜ እራስህን መፈልግ ትጀምራልህ ። ወድቆ ተነስቶ ነገሮችን ማየት እንደ ትልቅ እድል ሊታሰብ ይገባዋል። በውድቀቴ ጊዜ በቀለም የማልገናኛቸው ሰዎች የተጣመመውን ሕይወት አቃንተውልኛል። ዛሬ ከማደርገው መልካም ነገር ጀርባ እነዚህ ሰዎች አሉ።

እነዚህ ሰዎች ትዕግስትን አስተምረውኛል።  ትዕግስት ፍቅርን ና መዋደድን እንደሚያመጣ ፤ ሁሉም ሰው መወደድን እንደሚፈልግ ፍቅር መስጠት ግን ከባድ መሆኑን በህይወቴ ተምሬአለሁ ።  ሰዎች በሃሳብ  ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚገባና ለልዩነት መፍትሄው መነጋገር እና መተማመን  መሆኑን ፤ የሰው ልጅ እድገቱ ሀብት እና ትምህርት ብቻ ሳይሆን ከሰው ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በስራዐትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ  መሆን እንዳለበትና ለዚህም ሰው ለሰው ዋናው ቁልፍ መሆኑን  ትዕግስት ደግሞ ዋናው ዘዴ መሆኑን ህይወት አስተምሮኛል ።

**ማዕዶት** ፡ የውሰዱት ሀላፊነት ሰፊ ማሰተባበርና መምራትን ይጠይቃል የእርሶ እምነትና ዘዴ ምን ይመስላል? ብዙዎች እስካሁን ተሳክቶላቸዋል ይላሉ?

**ዶክተር አሻግሬ ፡** ሰዎች ላላቸው አመለካከት አመሰግናለው።  የበጎ እድራጎት  ስራ የአለቅነትና የታዛዥነት ሊሆን አይገባውም ። በእኔ ዕምነት መሪዎች ጥሩ ሲሆኑ የሚያከናውኑትን ስራ በሚገባ ጠንቅቀው የሚያውቁ ጥሩ ሰዎችን በዙሪያቸው ማሰባሰብ ይችላሉ። በበጎ አድራጎት አገልግሎት ወቅት ሰዎችን ማክበርና ማቅረብ እንዲሁም ሥራውን እየሰሩ ማሰራትና ለሥራው በቂ ትኩረትና ጊዜ መስጠት ለሌሎችም አርአያ መሆን ያሰፈልጋል;።

**ማዕዶት** የቤተክርስትያናችንን ግንባታና አካሄድ በሚመለከት  ራዕዮይዎ ምንድነው?

**ዶክተር እሻግሬ** ፡ በአጭር ግዜ ውስጥ የቤተክርስትያኗ ግንባታ ተጠናቆ ማየት እንዲሁም ቤተክርስትያናችን የምታደርገውን ሀይማኖታዊ ድጋፍ በማስፋት ማህበራዊ ግልጋሎት ሊሰጡ የሚችሉ የተለያዩ ስራዎችን ለምሳሌ የህጻናቶቻችን እና የአዛውንቶቻችን እንዲሁም የቤተክርስትያኗን ድጋፍን የሚፈልጉ ወገኖችን ችግሮች ለማገዝ የሚችሉ አልግሎቶች ተዘርግቶ ማየት ።

**ማዕዶት** ፡የተሰማሩበት አገልግሎት ረዘም ላለ ጊዜ ሊሄድ የሚችልና ሰፊ ሥራም የሚጠይቅ ነው ሥራውን ለማጠናቀቅ ቁርጠኝነቶ ምን ያህል ነው?

**ዶክተር እሻግሬ፡** ለአምላክ የምታደርገው ነገር ሊወሰን አይገባውም አምላክ ጤንነቱን ከሰጠኝ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ ጭብጨባ በአንድ እጅ አያምርም በሁለትና ከዛ በላይ ባሉ እጆች ነው የሚያምረው ሁላችንም አብረን እናጨብጭብ ነው የምለው። በአራዶች ቋንቋ እንደሚባለው እንዱዓለም አንዴ ማኖ አስነክቶኛል ስኬትን እስካይ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ። ባለቤቴ አንዷዓለምን ባገኘችው ቁጥር እኔን ወደ ቤተክርስትያን አገልግሎት እንድገባ ስላደረገኝ  ታመሰግነዋለች ከጎኔ በመሆን የምትረዳኝንና የምትደግፈኝን  ባለቤቴን ሰርካለም ደምሴን በጣም አመስግናለሁ ሰላሙን ሁሉ እመኝላታለሁ ። ተቆጥታም ተናዳም  ተጋፍታም ዛሬ ለሆንኩት ሰው ትልቁን ሚና የተጫወተች ነች።

# እንኳን ደስ አላችሁ

ምርቃት በማህበረሰቡ ውስጥ  ጠለቅ ብሎ የገባ ቅልብጭ ያለ ቋንቋ ሲሆን ይዘቱ መልካም ባህርይን ፤ ጥረትን ፤ መልካምነትንና የብስለትን መንገድ ያሳያል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ሀገራቸውን እና ወላጆቻቸውን የሚያከብሩ የተመረቁ ዜጎች በማፍራት የተለየ ቦታ እንደአላት ታሪክ ይመሰክራል። የቤተክርስትያኗ ልጆች የዛሬዋን ሀገራችንን እዚህ ለማድረስ ከፍተኛ አስተዋጻኦ ያደረጉ ሲሆን እንደዛሬው ትምህርት ቤቶች ባልነበሩበት ዘመን የቤተክርስትያን አባቶች በዛፍ ጥላ ስርና በየበረንዳው ፊደል ሲያስቆጥሩ የማንበብን አቅም ሲያዳብሩ ኖረዋል።  የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በትምህርት የምታምንና ልጆቿ በትምህርት እንዲበረቱ የምታበረታታ ሲሆን ዛሬም በስደት ልጆቿን ተከትላ ህይወታቸው የተቃና ፤ታሪካቸውን እና ሀይማኖታቸውን የሚጠብቁ ዜጎች እንዲሆኑ መንፈሳዊ ትምህርትን በመመገብና በማበረታታት ከፍተኛ ግልጋሎት በመስጠት ላይ ትገኛለች ።  በደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ደብር ተባርከው ትዳር በመሰረቱ ወላጆች እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት  ደብሩን ከተቀላቀሉ ምዕመናን አብራክ የተገኙ ፤ በቤተክርስትያኗ የህጻናት እና የመንፈስ ትምህርት ቤት ተኮትኩተው ያደጉ ወጣቶች ከኮሌጆችና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲመረቁ ማየት የወላጆች ብቻ ሳይሆን የቤተክርስትያኗ እና የምዕመኗ ደስታ ሲሆን በ2017 ዓ/ም ከተለያዩ ኮሌጆች ለተመረቁ ወጣቶች ማዕዶት እንኳን ደስ ያላችሁ ትላለች። ወደ ኮሌጅ ለሚገቡት የተባረከ የትምህርት ጊዜ ፤ ወደ የሥራ አለም ለሚሰማሩት መልካም የሥራ ጊዜ እንዲሆንላቸው  ወላጆችም ፀሎታቸው ደርሶ ይህንን ለማየት በመቻላቸው እንኳን ደስ አላችሁ እያለ ችሎታችሁ ለቤተክርስትያናችን የህንጻ ግንባታ ሂደት ተፈላጊ በመሆኑ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ጥረቱን እንድታግዙ የሕንፃ አስተባባሪ ኮሚቴ  ለምርቃኑ ጥሪ ያቀርባል።

## የ2017 የትምህርት ዓመት ምሩቃን

አንተነህ ይገርማል
ኤልሻዳይ ጌትነት
እምነት ሰሜ
እስቴ ይገርማል
ሄርሜላ ነጋሽ
ሁናቸው ገብረሰንበት
ቅድስት ኪካ
ቅዱስ ሠናይ
ኪሩቤል ሀይለማርያም
ሊዲያ አያሌው
ማህደር ጸጋዬ
ምስጋና አማረ
ሩት ሀይለገብርኤል
ጽዮን ጌታቸው

# የተግባር ሰዎች በታርጌት ፊልድ ስቴድዮም

የደብረ ሰላም ምዕመናን የመድኃኔዓለምን ቤት ለማነፅ በገንዘባቸው ፤ በእውቀታቸው እና በጉልበታቸው ከፍተኛ ሰራዎችን ለመስራት ቆርጠው ከተነሱ ቀናት አስቆጥረዋል ። የቤተክርስትያኑ ምዕመናን ይህ ከፍተኛ ስራ ተተግበሮ ለማየት ቀናኢ በመሆናቸው የሚያደርጉት እርብርብ ታሪካዊ ፤ ህብረታቸው የሚያኮራ ፤ በምዕመናኑ መካከከል ያለው ፍቅር የሚያስቀና፤ የሚያስመሰግን እና የክርስትያን ባህርያትንም የተላበሰ ነው። የቤተክርሰትያኑ የሕንጻ አስተባባሪ ኮሚቴ ከዘረጋቸው ተግባራት መካከል በታርጌት ፊልድ ስታዲዮም የበጎ አገልግሎት በመስጠት ገቢ ማስገኘት ሲሆን ይህን ሥራ ለማከናወን የቤተክርስትያኑ ምዕመናን ለሥራው የሚያበቃውን ስልጠና ወስደው  በሚፈልጉት ቀናት እየተገኙ ግልጋሎት በመስጠት ለግንባታው የሚያግዝ ገቢ ማሰገኘት ከጀመሩ ወራት  የተቆጠሩ ሲሆን ማዕዶት የፕሮግራሙ ተካፋዮችን የአንድ እሁድ ውሎን በታርጌት ፊልድ ተከታትላ ነበር።




የበጎ አገልግሎት የሚሰጡ ምዕመናን በአውቶቢስ እና የጋራ መኪና በመጠቀም ለሰራተኛ በተዘጋጀው በር ወደ ስታዲዮሙ ሲገቡ በእጃቸው የያዟቸው ቦርሳዎች፤ በጀርባቸው ያነገቷቸው ባክ ፓክስ ተበርብረው በስቴዲዮሙ አምስተኛ ፎቅ ላይ በተወሰነላቸው ስፍራ ከጠዋቱ አስር ሰዓት ላይ በመገኘት አንድ ሰዓት ቀደም ብለው ከገቡት የዕለቱ የቡድን አስተባባሪ ጋር ተገናኙ።  አስተባባሪው በዕለቱ ለሽያጭ የሚቀርቡትን ልዩ ልዩ ምግቦችና መጠጦች እንዲሁም ለሽያጭ የሚያስፈልጉትን  እቃዎች ቆጥረው ተረከበው የዕለቱን ስራ ለሌሎች ለማስረዳት ሲዘጋጁ ተሳታፊዎቹ በዕለቱ የሥራ ልብስ ፤ በቀይ ባርኔጣ ፤  በሰማያዊ ኮት አና በጥቁር ሱሪ  ተመሳስለው ለስራው መሟሟቅ ጀመሩ።፡ በዕለቱ  የሥራ ልብስ የተዋቡ የመድኃኔዓለም ምዕመናን 27 ሲሆኑ 20 ሴቶች 6 ወንዶች ነበሩ  የዕድሜ ስብጥሩም እንዲሁ የተለያየ ነበር።  የእለቱ አስተባባሪ የሥራ ምድብን ካብራሩ በኋላ ሁሉም ምድብ ምድቡን ያዘ። ገንዘብ ተቀባዮች ፤ ረዳት ገንዘብ ተቀባዮች (runners) ፤ አብሳዮች ወደ ምደብ ሥራቸው ተፍ ተፍ ማለት ጀመሩ ወዲያውም

የዕለቱን ግጥሚያ ለማየት የሚገባው ተመልካች ወደ ስቴድዮሙ መግባት ሲጀመር ምዕመናኑ በስራ ተጠመዱ ግማሹ አይስክሪም ዝቆ ይሰጣል ግማሹ ሆት ዶጉንና በርገሩን ይጠበሳል ግማሹ ዳቦ በማዘጋጀት ከቻፕና ሰናፍጭ ያደርጋል ሌላው ለሰላሳ ና ውሃ ያቀብላል ቢራ የሚቀዳው አረፋ ላለማብዛት ይሞክራል ግማሹ የመጀመሪያው በመሆኑ ካለው እሩጫ ጋር እራሱን ለማስተካከል ሲፍጨረጨር ግማሹ ተጠቃሚው ብዙ እንዳይቆም መልዕክት በማስተላለፍ እና ተጣድፎ በመስራት የበኩሉን ያደርጋል ። ትዕዛዝ መቀባበያው እና በመካከል የሚደረገው ንግግር የሀገር ቋንቋ የበዛበት ሲሆን መልዕክት ለማስተላለፍ አክብሮትን ፤ ስምን ለመጥራት ቁልምጫን መጠቀም ይሰተዋል ነበር ። የተሳታፊዎቹ ትብብር የሚያስቀና እና ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን የተሞላው ነበር ። አልፎ አልፎ የአነጋገር ዘይቤ ና የሚከሰቱ ድርጊቶች ለፈገግታም ይዳርጉ ነበር ። ተሳታፊዎቹ የመጡበትን አላማ ለማከናወን ደፋ ቀና በሚሉበት ወቅት በስታድዮሙ የታደሙ ተመልካቾች ቡድናቸው በለስ እንዲቀናው ድጋፋቸውን ሲሰጡ እና ነጥብ ሲቆጠር ስሜታቸውን በመደሰት ሲገልጹ ቆይተው የከተማችን ቡድን በለስ ሳይቀናው ጨዋታው ሲጠናቀቅ ተመልካቹ በመጣበት መልኩ ስታድዮሙን ለቆ ሲወጣ የመድኋኔዓለም ልጆች የሰሩበትን ዕቃ እና መሳሪያ በማጽዳት ላይ ተሰማሩ። ከጥቂት ጊዜያት በፊት በድምጽ የታጀበው ስታዲዮም በጸጥታ ተወርሶ ድምጽ አልባ ሲሆን የመድኋኔዓለም ልጆች የተሸጠንና የተረከቡትን ከተሰበሰበው የሽያጭ ገንዘብ ጋር ማመሳከር ተያያዙት ይህ ሥራ በትዕግስትና በትክክል መሰራት ያለበት በመሆኑ የቡድኑ አስተባባሪና የተወሰኑ ፈቃደኞች ጓዶቻቸውን አሰናብተው ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ስራውን በሚገባ በመስራት ግዴታቸውን ተወጥተው እንደሌሎቹ ጓደኞቻቸው ቆሞ የዋለን ጉልበት እና ወገብን ለማሳረፍ ወደ ቤታቸው ሲያዘግሙ የመድኋኔዓለምን ቤት ለመስራት የሚደረገውን ጥረት በማገዛቸው ውስጣቸው በደሰታ መሞላቱን ከፊታቸው ይነበብ ነበር።






## ይቀጥል መንፈሱ

ይቀጥል መንፈሱ ይህ አንድነታችሁ
የፀና እምነታችሁ ይህ ትብብራችሁ
ታሪክን ለማደስ የትውልድ ድርሻችሁ
ፅኑ ዕምነታችሁ ሥራችሁ ብሩኩ
ይቀጥል ይበርታ በእግዚሔር ተባረኩ
መስቀሉ ተሰቅሎ ቆሞ ጉልላቱ
ሲገባ እቤቱ ሚስጥረ ታቦቱ
ህልማችሁ ይፈታል ይሆናል እውን
ጠንከር ያለ ዕምንት ካለ መታመን
ይባርካችሁ እሱ በፍቅር በፀጋ
ሰላም በረከቱ ይሁን ከእናንተ ጋ
የላሊበላ አክሱም የክርስቶስ ልጆች
የጎንደር አድባራት ዋልደባ ገዳሞች
የቁልቢው ገብርኤል የግሸን ማርያም
ታሪክ በረከታቸው ይቀጥል እዚህም
በክርስቶስ ልጆች በመድኃኔዓለም

# የደብረ ሰላም ቤተክርስትያን ከየት ወደ የት

የዛሬው መድኃኔዓለም ቤተክርስትያን አሁን ያለበት ደረጃ ለመድረስ ሰፊ ዓመታት ያሳለፈ ሲሆን የዚህን ታላቅ ደብር ታሪክ ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ እና እንዲሁም  በተለያዩ ጊዜያት የቤተክርስትያኑ ተገልጋይ የሆኑ ምዕመናን ያልደረሱበትን እና ያላዩትን የቤተክርስትያኗን ታሪክ እንዲያውቁ ማደረግ ተገቢም በመሆኑ በቤተክርስትያኑ ታሪክ ላይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቻው ግለሰቦች በማነጋገር  የቤተክርሰትያኗን ታሪክ በየደራጃው በተከታታይ ይዘን እንቀርባለን። ይህን የመጀመሪያ ዓምድ ለማዘጋጀት  የቤተክርሰትያኗ መስራች እና እንጋፋ አባላት አቶ ዘውዴ ኃይሉ እና አቶ ዕድል ሡናይ ላደረጉት አስተዋጾ ማዕዶት ምስጋና ታቀርባለች።

በ1980 ዎቹ ዓመታት ሚኒያፖሊስና ሴንትፖል የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አነስተኛ ሲሆን የነበሩትም ተራርቀው ነበር የሚኖሩት ። በዛን ጊዜ አዳዲስ የሚመጡ  ኢትዮጵያውያን   እንግዶች ከነባሮቹ የሚተዋወቁት የመገናኛ ቤታቸው የዛሬው የኢትዮጵያ ሬድዮ አዘጋጅ አቶ አህመድ ዋሴ ቤት ነበር።   ግንኙነቱ በአብዛኛው በማህበራዊ ግንኙነት ላይ ያተኮረ ነበር ። ቤተክርስትያን የማቋቋም ሀሳብ የራሱ ሂደት የነበረው ሲሆን ሂደቱን በሚመለከት አቶ ዘውዴ ኃይሉ እንዲህ ይላሉ።

“ ዓመት በዐል በሚሆንበት ጊዜ የመሰባሰብ ፍላጎት እና የቤተሰብ ፤ የወገን እና የሀገር ፍቅር ስለሚያይል አንዳንዶቻችን ዳቦ ሌሎቻችን ኬክ እንዲሁም የሚጠጣውን በመያዝ በጋሼ በትረ ቤት እንታደማለን ። ጋሼ በትረም የተለያዩ የሚጣፍጡ ምግቦች አዘጋጅቶ ቆሞ ያስተናግደን ነበር ። ጋሼ በትረ  የቤተክርስትያን ዕውቀት ካለው  ቤተሰብ የወጣና አባቱም በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን የታወቁ ሰው የነበሩ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ የሀይማኖት ዕውቀትም የነበረው በመሆኑ የተለያዩ ጥቅሶችን በማጣቀስ ያስተምረን ነበር ። አልፎ አልፎም መጽሐፍ  ቅዱስን ተንተርሶ  ሰፊ ትምህርት በማካፈል የተጣላ ያስታርቅ ነበር። ታዲያ በአንድ ፋሲካ እዛው ጋሽ በትረ ቤት ታድመን ለምን ግሪክ ቤተክርስትያን ሄደን አናስቀደስም የሚል ሀሳብ በማቅረቡ በእርሱ አነሳሽነት ግሪክ ቤተክርሰትያን መታደም ጀመርን። >>

ሂደቱ  ቀጥሎ በጊዜው በአካባቢው የነበሩ  ኢትዮጵያውያን ነጭ ልብሳቸውን በመልበስ ዘወትር እሁድ በግሪክ ቤተክርስትያን የፀሎት ግልጋሎት መከታተል ጀመሩ። የግሪክ ቤተክርስትያን ሀላፊዎች አውደ ምህረታቸውን ኢትዮጵያውያኑን ለሃዘንም ለሰርግም እንዲገለገሉበት በማድረግ ሀይማኖታዊ ወገንተኝነታቸውን አሳይተዋል። አቶ ዘውዴ ሀይሉና ባሌቤታቸው በጋብቻ የተባረኩት በዚሁ ቤተክርስትያን ሲሆን የግሪክ ቤተክርስትያን ለቤተክርሰትያናቸን መጠንሰስ እና ለ ኢትዮጵያውያን መሰባሰብ  አስተዋጾ ባለውለታ ነች ማለት ይቻላል።  የሚሰባሰበው ምዕመናን ቁጥር እየበረከተ ሲሄድ አቶ በትረ ለኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ስርዐት ቀረብ ያለው የግብጽ ቤተክርስትያን ነው በማለት ሰላሳሰቡ ሴንትፖል ወደሚገኘው የግብጾች ቤተክርሰትያን መሄድ ተጀመረ። ስርዐቱ ተመሳሳይ በመሆኑና የቤተክርስትያን ስሜት እየጎለበተ በመሄዱ በየሳምንቱ የሚታደመው ሰው እየበረከተ ሄደ በዛን ወቅት የቤተክርሰትያን ዕውቀት ከነበራቸው ሰዎች መካከል የእነ እቶ ዕድል አባት አቶ ሰናይ ቦጋለ አንዱ ሲሆኑ አቶ ሰናይ ድቁና የተማሩ ፤ ድጓ ያነበቡ ፤ ቅኔ  የተቀኙ የመጽሐፍ ትርጓሜ የተከታተሉ በመሆናቸው የቤተክርስትያን ስርዐት ሰለሚያውቁ በማብራራት ያበረታቱ ነበር። በዚህ ቤተክርስትያን አንድ የፋሲካ በዓል ኢትዮጲያዊያኖች በነጭ ልብስ ደምቀው መታየታቸው አንዳንድ ግብጻዊያንን በማስደንገጡ የቤተክርስትያኑ አስተዳዳሪ ቄስ አባጊዮርጊስ ከአቶ ዘውገ ፤ ከአቶ ታየ እና ከአቶ ዘውዴ ጋር በመገናኘት “ለምን የራሳችሁ የፀሎት ቦታ አታመቻቹም እንደውም የግብጹ ፓትርያክ  አቡነ ሻየድ ኢትዮጵያኖች በአካባቢህ ካሉ ዕርዳቸው ብለውኛል ቦታ ከያዛችሁ መጥቼ እባርካቹሀለሁ  ብለው አበረታቷቸው።

ይህን ዜና ለአቶ በትረ ሲያወጡና ሲያወርዱት የነበረውን ሀሳብ ይበልጥ ሲያጠናክርላቸው ‘’ጌታ በስሜ አንድም ሁለትም ሆናችሁ በተሰባሰባችሁበት  ሁሉ በመካከላችሁ እገኛለው”’  ብሏል ጌታ ከጎናችን ነው ልንገፋበት ይገባል ሲሉ አቶ ታየ በታሪክ ልዩ ስፍራ ያላት ቤተክርሰትያን በከተማቸን መኖር ለኛ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካን አሜሪካን ጭምር ትልቅ ኩራትም ነው በማለት ሀሳቡን አጎለበቱት በዚህ መሰረት የመጀመሪያውን ታሪካዊ ስብሰባ በአቶ በትረመኖሪያ ቤት ለማድረግ አቶ በትረ ለአቶ ታየ ረታ፤ ለአቶ ዘውዴ እና ለአቶ ተገኘ ጥሪ አደረጉ።

«ይህ በዚህ እንዳለ እንደገና በግሪክ ቤተክርስትያን መሰባሰብ ተጀመረ ። ግሪኮቹም አንድ ክፍል ሰጡ ፤ የተወሰኑ ሰዎች አባ ኪሮስ የሚባሉ መነኩሴን በመያዝ የቅዳሴ ስርዐት ጀመሩ ዲያቆንም እሳቸው ነበሩ ስረዕተ ቁርባን የነበረ አይመስለኝም ።፡ጋሼ በትረም ደስ አለው ከማህላችን ጠለቅ ያለ ዕውቀት የነበረው እሱ ሰለነበረ ቅዳሴውን በመቀበል ያግዝ ጀመር። ቁጥራቸን ከሃያ አይበልጥም  ወ/ሮ እንዬ ፤ አቶ ዕድል እስከ ባለቤቱ ፤ ገሊላ ሚሊዮን ፤ አቶ መንግስቱ ፤ አቶ አጥናፉ፤ አቶ ታየ ፤  ህገ መንግሰት፤ አቶ ኤርምያስ ፤ አቶ ተስፋሁን ፤ አቶ ተገኝ ወ/ሮ አልማዝ እና አቶ ንጉሴ ከነበሩት መሃል ናቸው።  በዛን ጊዜ  የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ያለመኖር የቀሰቀሰውን ስሜት በሚመለከት አቶ ዕድል ,<< አንድ ቀን በሰሜን ምስራቅ ሚንያፖሊስ በሚገኘው በሴንት ማይክል ቤተክርስትያን በኩል እኔና ቤተሰቤ ስናልፍ ወደ በሩ ጠጋ ብለን የግል ፀሎት ለማድረስ ስንጀመር  በዛው አካባቢ የነበሩ የቤተክርስትያኑ አባል ጥፋት የምናደርግ መሰሏቸው ውሻ ላኩብን በዚህን ጊዜ ባለቤቴ ወ/ሮ ኤፍራታ ስቅ ስቅ ብላ አለቀሰች >> በማለት በትዝታ ተወስደው አይናቸው እንባ አዝሎ በስሜት እያነቡ አጫውተውናል።   ---------------ይቀጥላል።

# «ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው»

ይህን ቃል የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን የቃሉ ማደሪያ የሆነችው ቤተክርስትያናችን ህጻናትን በመንፈሳዊ ሕይወት አንጾ በመኮትኮት የጌታን ቃል በተግባር በመተርጎም መልካም ስራ እየሰራች ትገኛለች። ቤተክርስትያናችን ከሐምሌ 3 እስከ 7 ለህጻናት የሳመር ካምፕ በማዘጋጀት በርካታ ህጻናትን ያስተናገደች ሲሆን ህፃናቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በመከታተል  የተማሩትን ትምህርት በፅሁፍ ወይም በስዕል በመግለጽ እንዲሁም የግል ችሎታቸውን ለሌሎች በማሳየት እና በተለያዩ  ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች እና የቡድን ጨዋታዎች ላይ በመሳተፍ የከረሙ ሲሆን የቁርስ እና የምሳም አገልግሎት ተሰጥቷቸዋል። በዚህ አጋጣሚ ይህን ፕሮግራም ላዘጋጁ ምዕመናን ያለንን አክብሮት እየገለጽን የቤተክርስትያናችን የህንጻ ግንባታ የሕጻናት እና የወጣቶችን መንፈሳዊ ትምህርት እና ግልጋሎትን  ለማሳደግ ወሳኝ በመሆኑ የልጆቻችንን የወደፊት ዕጣ ለመወሰን በግንባታው ላይ ሁላችንም የበኩላችንን እንድናደርግ በሕጻናቱ ስም እንጠይቃለን።




ማዕዶት

የዛሬ 20 ዓመታት ለቤተክርስትያናችን ዓምድነት የተመረጠችው ማዕዶት ዛሬም የቤተክርሰትያናችንን ግንባታ ሂደት ለማገዝ ብቅ ብላለች። ማዕዶት ማለት መሸጋገሪያ ወይም ድልድይ ማለት ሲሆን በዓምድነት የሰየሟት የወቅቱ የቤተክርስትያናችን አስተዳዳሪ  የነበሩት አቡነ ዳንኤል ናቸው ። ይህ የዛሬው ዕትማቸን 5ተኛው ሲሆን በየሶስት ወሩ ብቅ እንድትልም ዕቅድ ተይዞላታል። አስተያየት በመስጠት እና በመሳተፍ እንድታግዟት ትጠይቃለች ።

# የሕንጻ አስተባባሪ ኮሚቴ እንቅስቃሴ አጭር ሪፖርት

የሕንጻ ግንባታ ኮሚቴ በየወሩ በሁለተኛው ቅዳሜ በሁለት ሰዓታት እንዲጠናቀቁ የያዛቸው ስብሰባዎች አባላቱ ከፍተኛ ትጋት ፤ ትኩረት እና ፍላጎት በተሞላበት በሚያደርጉት ሰፊ ውይይቶች የተነሳ ከተያዘላቸው ጊዜ ተጨማሪ ሰዓታት እየታከለባቸው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በመምከር ሳይቋረጥ የተደረገ ሲሆን በእነዚህ ስብሰባዎች የውሳኔ ሐሳቦችን በማዘጋጀት ለቤተክርስትያኑ የሥራ አመራር ቦርድ በማቅረብ ውሳኔዎች እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡ በኮሚቴው ስር የተዋቀሩት አራቱ ንዑሳን ኮሚቴዎች ያከናውኑት ስራ በሚቀጥለው መልኩ ተጠናቅሮ ቀርቧል።

**የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ**

- በመጋቢት ወር የመጀመሪያውን ጋዜጣ አዘጋጅቶ አሰራጭቷል
- የኤዲቶሪያል ቦርድ አቋቁሞ ጋዜጣው ሰፋ ያለ ዓምድና ጠለቅ ያለ ይዘት ባለው መልኩ የሚዘጋጅበትን ሁኔታ ነድፎ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል።
- የሶሻል ሚዲያ ድህረ-ገጽ አጠቃቀም መመሪያ ምን መምሰል አለበት የሚል መረጃ አዘጋጅቶ በሕንፃ አስተባባሪ ኮሚቴ በኩል ለቦርዱ አቅርቧል። በቅርቡም ለግንባታ ኮሚቴ እንቅስቃሴ ፌስ-ቡክን ለመጠቀም እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡
- የአስተያየት መስጪያ ሳጥን አዘጋጅቷል
- ከጋዜጦች፤ ከድህረ-ገጽ አዘጋጆች እና ከኢትዮጵያ ሬድዮ ጋር ግንኙነት ፈጥሯል፡፡

**የፋይናስ ኮሚቴ**

- የራሱ የሆነ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ አዘጋጅቶ ጥቅም ላይ አውሏል፡፡
- የተለያዩ ሸቀጦችን ለሽያጭ በማቅረብ ገቢ በማሰባሰብ ላይ ይገኛል ።
- ከአባላት መዋጮ፣ ከሽያጭ እና ከልዩ ልዩ ምንጮች የተገኙትን ገቢዎች በአግባቡ ሰብስቦ በተከፈተው የባንክ አካውንት ገቢ አድርጓል፡፡

እስከ ኦገስት 2017 ድረስ የተሰበሰበው የገቢ መጠን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| | የገቢ ምንጭ | የተሰበሰበ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ከአባላት ለሕንፃ ግንባታ ቃል የተገባ | $127,144 | 00 |
| 2 | የሱቅ ሽያጭ | $28,869 | 56 |
| 3 | ስጦታ | $29,977 | 80 |
| 3 | ከተለያዩ የገንዘብ ማስገኛ ዝግጅቶች እና የምግብ ሽያጭ | $16,104 | 00 |
| 4 | ከታክስ አገልግሎት | $2680 | 00 |
| 5 | ከታርጌት ፊልድ | $38,839 | 35 |
| 6 | ከሳንቲም ሳጥኖች | $2543 | 84 |
| 7 | ጁላይ 29 በተድረገው ዝግጅት የተሰበሰበ | $13,702 | 05 |
| 8 | ጠቅላላ | $259,860 | 60 |

**የግንባታ ኮሚቴ**

- የምንገነባው ሕንፃ ምን መምሰል አለበት በሚል ከአባላት የሰባሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል።
- የሕንፃ ዲዛይን ተቀራጮችን በማወዳደር ATS&R የሚባል የአርክቴክቸር ድርጅት መርጦ ከድርጅቱ ጋር የተለያዩ ውሎችን ለመፈራረም በጥናትና ዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም በእርዳታ(pro bono) የሚሰራ ጠበቃ በመያዝ ከድርጅቱ ጋር የሚደረገው ውለታ የቤተክርስትያኑን ጥቅም የሚጠብቅ እንዲሆን ጥረት እያረገ ሲሆን ተቋራጩ አምስት የሚሆኑ የሕንፃ ዲዛይኖችን ለአማካሪው እንዲያቀርብ ግፊት እያደረገ እና እንደ አማራጭ የተለያዩ ዲዛይኖችን ችሎታው ባላቸው የቤተክርስትያኑ አባላት እንዲሰሩ በማድረግ እና በዲዛይን ውስጥ ሊካተቱ ስለሚገባቸው ሥራዎች ከካህናቱም ምክር እየተቀበለ ነው፡፡

**የገንዘብ ማስገኛ ኮሚቴ**

- ከሒሳብ ኮሚቴ ጋር በመሆን ሳምንታዊ ሽያጮችን በማከናወን ይገኛል
- በወንዶች የቤተክርስትያኑ አባላት የቁርስ ፕሮግራም በማዘጋጀት ገቢ አሰባስቧል
- በታርጌት ሜዳ የነፃ አገልግሎትን በማስተባበር ከ200 በላይ የሚሆኑ አባላት ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ እስከ ወሩ መጀመሪያ በ16 ጨዋታዎች አገልግሎት ሰጥተዋል፡፡ በአማካይ 24 ሰዎች በቀን በማሳተፍ እስከ ጁላይ 2017 መጀመሪያ 180 አባላት የፕሮግራሙ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡
- እስከ ጁላይ 2017 መጀመሪያ 83 አባላት ለአንድ ጊዜ፤ 41 አባላት ሁለት ጊዜ፤ 29 አባላት ሶስት ጊዜ ፤ 18 አባላት አራት ጊዜ ፤ 5 አባላት አምስት ጊዜ ፤ 2 አባላት ስድስት ጊዜ እና 1 አባል ሰባት ጊዜ ነፃ አገልግሎት በመስጠት በአማካይ 25 ሺ ዶላር አስገኝተዋል፡፡
- በቅርቡም በዩኤስ ባንክ ስታድዮም አገልግሎት ለመስጠት አባላት ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ ወደ ሥራ መሰማራት ተጀምሯል።

አባላት በፍቃደኝነት ለማዋጣት የገቡትን 5000.00 ዶለር የገንዘብ መዋጮ በሚመለከት እስካሁን 67 አባላት መዋጮ የጀመሩ ሲሆን ከነዚህም 10 አባላት ሙሉ በሙሉ ሁለት አባላት ከግማሽ በላይ 54 አባላት ደግሞ 2000 ዶላርና ከዛም በታች አዋጥተዋል፡፡ከ350 በላይ የሚሆኑት አባላት ግን ምንም አይነት ክፍያ አልፈጸሙም፡፡ አላማችንን ለማሳካት ከእያንዳንዱ አባል ቢያንስ በወር በአማካይ 150 ዶላር መዋጮ ይጠበቃል፡፡ ለምሳሌ በማርች ወር 15 አባላት እንዲሁም በጁን ወር 7 አባላት ክፍያ የጀመሩ ሲሆን በጁላይ ግን አዲስ መዋጮ የጀመረ አባል የለም ይህ የመዋጮ መረጃ እንደሚያመለክተው የአዲስ ከፋዮች ቁጥር በየወሩ እየቀነሰ መምጣቱ ሲሆን አሁን ባለንበት የገንዝብ ማሰባሰብ ፍጥነት ከአባላት በግምት የሚጠበቀውን ሁለት ሚሊዮን ዶላር በሶስት ዓመት ለማሰባሰብ አስቸጋሪ መሆኑን ኮሚቴው በመገንዘብ አባላት ቃል የገቡትን መዋጮ ለማሰባሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን በመቅረፅ ላይ ይገኛል፡፡

***ሆያ ሆዬ ሆ !***
***የቡሄ ብርሃን***
***ለእኛ መጣልን***
***ክፈትልን በሩን***
***የመድኃኔዓለምን***
***ዓመት ዓውደ ዓመት***
***ድገምና***
***ዓመት!***
***ድገምና***
***እንዲሁ እንዳለን***
***አይለየን***
***ህብረታችን በዝቶ ሆ!***
***ጥረታችን ሰፈቶ ሆ!***
***ሃሳባችን ሞልቶ ሆ!***
***ዳግም እንገናኝ ሆ!***
***ሕንጻችን ተሰርቶ ሆ!***
***ክበር በሥራ ክበር***
***በዕምነት***
***የመድኃኔዓለም ቤት!!***



የቡሄ (የደብረ ታቦር) በዓል በመድኃኔዓለም ቤተክርስትያን ሲከበር



# የቤዛ ኩሉ የሰንበት ትምህርት ቤት 21ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ከሕንፃ አሰተባባሪ ኮሚቴ ጋር በመተባበር አከበረ

የደብረ ሰላም መድኃኔለም የሕንፃ አሰተባባሪ ኮሚቴ እና የ21ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ያከበረው የቤዛ ኩሉ የሰንበት ት/ቤት በጋራ በመሆን በ 2629 30ኛ ጎዳና ሚኒያፓሊስ በሚገኘው ለቤተክርስትያናቸን የህንጻ ግንባታ ተከልሎ በተያዘው ሰፊ ግቢ ወስጥ በርካታ ምዕመናን ከነቤተሰቦቻቸው እና ወዳጆቻቸው እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ በተገኙበት ቅዳሜ ጁላይ 29/2017 በካህናት አባቶች ቡራኬ እና ቅዳሴ ፤ የቤዛ ኩሉ የስንበት ትምህረት ቤት አባላት ባቀረቧቸው መንፈሳዊ መዝሙሮች እና ያሬዳዊ ዝማሬዎች ፤ በዕለቱ ተጋባዥ እንግዳ በዲያቆን እስክንድር አሰፋ በተሰጠ መንፈሳዊ ትምህርት እና ለህጻናት በተዘጋጀ ልዩ ዝግጅት ደመቅ ተከብሯል።፡በዕለቱም ላለፉት አመታት በቤዛ ኩሉ የሰንበት ትምህርት ቤት ሰፊ ግልጋሎት ላደረጉ አባላት የምስከር ወረቀት ሲበረከት የምግብ እና የቶምቦላ ሽያጭ በማከናወን ለቤተከርሰትያን ግንባታ የሚውል ገንዘብ ማስገባት ተችሏል። የሕንጻ እስተባባሪ ኮሚቴ እና የሰንበት ትምህርት ቤቱ ይህ ፕሮግራም እንዲሳካ ጊዜያቸውን ፤ ገንዘባቸውን እና ጉልበታቸውን በመስጠት የተባበሩትን ቸሩ መድኃኔዓለም አብዝቶ እንዲሰጣቸው በመመረቅ ምስጋና እቅርበዋል።

